| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "መድበል ።" |
| ርእስ ፤ | "የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፥ አንቀጽ ፡ 260 ፡ እና ፡ አንቀጽ ፡ 261 ።" |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መጋቢት ፡ 2013 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2013-004 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |


# መድበል

archives | محفوظ

# የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፥ ቍጥር ፡ 260 ፡ እና ፡ ቍጥር ፡ 261 ።

[ከኢትዮጵያ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ (ገጽ ፡ 110-112) ፡ የተቀዳ ።

## ቍጥር ፡ 260 ፤ ያገሩን ፡ መከላከያ ፡ ኀይል ፡ በመንካት ፡ ስለሚሠራ ፡ ወንጀል ።

ማንም ፡ ሰው ፥ ኾነ ፡ ብሎ ፡–

(ሀ) ለጦር ፡ ሰራዊት ፡ የሚያገለግለውን ፡ ወይም ፡ ለሀገሩ ፡ መከላከያ ፡ የኾነውን ፡ ማንኛውንም ፡ የጦር ፡ ሰራዊት ፡ የሥራ ፡ ክፍል ፡ ኹሉ ፣ ቤቶችን ፡ ወይም ፡ የጦር ፡ ስፍራዎችን ፣ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ መስጫ ፡ መሣሪያዎችን ፡ ኹሉ ፣ የመመላለሻ ፡ መንገዶችን ፡ ወይም ፡ የዕቃ ፡ ማመላለሻ ፡ ተሽከርካሪ ፡ መኪናዎችን ፣ ማንኛዎችንም ፡ ጥበባውያን ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ የተቋቋሙ ፡ ፋብሪካዎችን ፣ ማከማቻዎችን ፣ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ኹሉ ፡ ያላግባብ ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠትና ፡ በማፍረስ ፣ በማሰናከል ፡ ወይም ፡ በከፊልም ፡ ኾነ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ እንዳያገለግሉ ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

(ለ) የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ዜጎች ፡ ለውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ወታደሮችን ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፣ ወታደሮችን ፡ በመቅጠር ፡ ወይም ፡ ለጠላት ፡ መንግሥት ፡ እንዲቀጠሩ ፡ መንገድ ፡ በመፈለግ ፡ ወይም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ችሎታ ፡ እንዳለው ፡ ለጠላት ፡ የመንግሥትን ፡ ጦር ፡ ሰራዊት ፡ በመቅጠር ፡ ወንጀልን ፡ የሠራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

(ሐ) የጦር ፡ ወታደሩ ፡ የጦር ፡ አገልግሎቱን ፡ ከመፈጸም ፡ እንቢተኛ ፡ እንዲኾን ፣ ሽብርን ፡ እንዲያነሣ ፡ ወይም ፡ እንዲከዳ ፡ በግልጽ ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ወይም ፡ የጦር ፡ ወታደርነት ፡ ግዴታ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ከእነዚህ ፡ ወንጀሎች ፡ አንደኛውን ፡ እንዲፈጽም ፡ በማደፋፈር ፡ ያነሣሣ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

(መ) ወይም ፡ በማንኛውም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ የተንኰል ፡ መንገድ ፡ ላገሩ ፡ መከላከያ ፡ የተመደበውን ፡ የጦር ፡ ሰራዊቱን ፡ የጥንቃቄ ፡ ድርጅት ፡ ያሰናከለ ፣ ያበላሸ ፡ ወይም ፡ ያፈረሰ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

እጅግ ፡ ቢያንስ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ በሚደርስ ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፤ ወይም ፥ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ቢኾን ፥ ይልቁንም ፡ በጦርነት ፡ ወይም ፡ ጦር ፡ አሥጊ ፡ በኾበነት ፡ ጊዜ ፡ የተፈጸመ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በሞት ፡ ፍርድ ፡ የቀጣል ።

## ቍጥር ፡ 261 ፤ ከፍ ፡ ያለ ፡ ክዳት ።

ማንም ፡ ሰው ፥ በትውልድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የኾነ ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ የተሰጠው ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥቅም ፡ እንዲያከናውን ፡ በግልጽ ፡ የታዘዘ ፡ ሰው ፡–

(ሀ) የጦር ፡ መሣሪያን ፡ በመያዝ ፡ ወይም ፡ በጸብ ፡ ሥራ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የተቃወመ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

(ለ) ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ጦርነትን ፡ ከሚያደርግ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ መንግሥት ፡ ጥቅም ፡ ከሚሠራ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ከተቋቋመ ፡ ክፍል ፡ ጋራ ፡ በመተባበር ፡ የስለላ ፡ ሥራዎችን ፡ የሠራ ፡ ወይም ፡ ምስጢራዊ ፡ ግንኙነትን ፡ በማድረግ ፡ ጠላት ፡ እንዲመቸውና ፡ እንዲቀናው ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ የረዳ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

(ሐ) ዕቃዎችን ፣ የጦር ፡ መሣሪያዎችን ፣ ዐቅዶችን ፡ ("ፕላኖችን") ፣ ማስረጃ ፡ የሚኾኑ ፡ ጽሑፎችን ፡ ወይም ፡ ለሀገሩ ፡ መከላከያ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ማንኛዎቹንም ፡ ነገሮች ፡ በቀጥታ ፡ ወይም ፡ በእጅ ፡ አዙር ፡ ለጠላት ፡ አሳልፎ ፡ በመስጠት ፡ ወይም ፡ በአገልግሎቶችና ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፥ ዕቃዎችን ፡ ለጠላት ፡ በማቅረብ ፡ ጠላትን ፡ የደገፈ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ከዐምስት ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ ልክ ፡ ሊደርስ ፡ በሚችል ፡ ጽኑ ፡ እስራት ፡ ወይም ፥ ነገሩ ፡ ከባድ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ በሞት ፡ ፍርድ ፡ ይቀጣል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2013 ፡ ዓ.ም. ።